በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

In the name of the father the son and the holy spirit one God Amen !

የጥምቀት መዝሙራት

1.† በፍሥሐ ወበሰላም†

በፍሥሐ ወበሰላም (፪)

ወረደ ወልድ (፬) ወልድ ውስተ ምጥማቃት (፪)

2.† ወረደ ወልድ †

ወረደ ወልድ(፫)×፪

እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት(፪) ×፬

3.† ሖረ ኢየሱስ†

ሖረ ኢየሱስ ሖረ ኢየሱስ(፪)

እም ገሊላ ኀበ ዮሐንስ(፪) ×፬

ሔደ ኢየሱስ ሔደ ኢየሱስ (2)

ከገሊላ ወደ ዮሐንስ (2)×4

4.† ኢየሱስ ሖረ †

ኢየሱስ ሖረ ሀገረ እሴይ(፪)

ዮሐንስ አጥምቆ በማይ (፪)×፬

5.† እግዚኡ መርሐ †

እግዚኡ መርሐ ዮርዲያኖስ አብጽሐ (፪)

ወበህየ ዮሐንስ ወበህየ ፍፁመ ተፈስሐ (፪)

ጌታውን መራና ዮርዲያኖስ አደረሰው(2)

በዚህም ዮሐንስ በዚህም ፈጽሞ ደስ አለው (2)

6.† ኀዲነ ተስዓ †

ኀዲነ ተስዓ ወተስዓተ ነገደ ነገደ (፪)

ማዕከለ ባህር(፬) ቆመ ማዕከለ ባህር (፪)

7.† ኧኸ ኀዲነ ተስዓ†

ኧኸ ኀዲነ ተስዓ ኧኸ ወተሰዓት ነገድ (፪)

ኧኸ ማዕከለ ባህር ቆመ ማዕከለ ባህር (፪)

8.† ዮሐንስ አትመቆ ለኢየሱስ(፪)

በፈለገ ዮርዲያኖስ በፈለገ ፈለገ ዮርዲያኖስ(2)

9.† መጽአ ቃል †

መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል (፪)

ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር(፪)

መጣ ቃል ከደመና እንዲህ የሚል (2)

የምወደው የማፈቅረው ልጄ ይህ ነው(2)

10.† ተጠምቀ ሰማያዊ†

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ(2)

ተጠምቀ ሰማያዊ በዕደ መሬታዊ (2)

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ (2)

አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በልደትህ

አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በጥምቀትህ

11.† ወተመሰሎ †

ወተመሰሎ ሰባዐ ዓይነ አባግዐ ላባ ወማይ(2)

ለኀበ አባግዕ ዘዮም (2) ወጥምቀት ዐባይ(2)

12.† ነድ ለማየ ባህር †

ነድ ለማየ ባሕር ከበቦ(፪)

ማየ ባሕር ኀበ የሐውር ጸበቦ

ማየ ባሕር ኀበ የሐውር ከበቦ(፪)

13.† ዮሐንስኒ ሀሎ†

ዮሐንስኒ ሀሎ ያጠምቅ (፪)

በሄኖን በቅሩበ ሳሌም (፪) ×፬

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

In the name of the father the son and the holy spirit one God Amen !

14. † እንዘ ሕፃን †

እንዘ ሕፃን ልሕቀ በዮርዳኖስ ተጠምቀ (2)

በዮርዳኖስ (2) ተጠምቀ በዮርዳኖስ (2)

ትርጉም ሕፃን ሆኖ ጥቂት በጥቂቱ አደገ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

15. † በዕደ ዮሐንስ †

በዕደ ዮሐንስ ተጠምቀ ኢየሱስ ናዝራዊ(2)

ሰማያዊ (5) ኢየሱስ ናዝራዊ /ዕደ መሬታዊ/

ትርጉም ሰማያዊው የናዝሬቱ ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

16. † ግነዮ ለእግዚአብሔር†

ግነዮ ለእግዚአብሔር እስመ ሔር (2)

እስመ ለዓለም ምህረቱ እስመ ለዓለም (4)

እናመሰግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ (2)

የዓለም ቤዛ ነውና የማህፀንሽ ፍሬ (4)

ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ካንቺ ተወልዶ(2)

መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ (2)

በድንግልናሽ የወለድሽው ክርስቶስ (2)

የድኩማኖች ብርታት ነው የህሙማን ፈውስ (4)

በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ እዳችን ፋቀ (2)

በቸርነቱ ጠብቆ ከበደል አራቀን(4)

ስምሽን የጠራ ዝክርሽን ያዘከረ (2)

በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ (4)

ብርሃን መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ (2)

ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ (4)

እመቤታችን እናታችን ማርያም (2)

የተማፀነሽ ይድናል ለዘለዓለም (4)

ድንግልናሽ ሳይለወጥ ወለድን የወለድሽ (2)

የጌታችን እናት ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ

የጌታችን እናት ማርያም ንጽሕት አንቺ ነሽ

17. † በጎል በጎል †

በጎል በጎል ሰበዐ ሰገል (4)

በጎል ሰብዐ ሰገል ሰገዱለት (4)

ፀሐይ (2) ፀሐይ ሰረቀ (2)

ፀሐይ ሰረቀ ክርስቶስ ተጠምቀ (4)

አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ (4)

የእግዚአብሔር መንፈስ ከላይ ወርዶልሽ

የዓለም መድኃኒት ተጠመቀብሽ

ድንግል ማርያም ንጽሕት ቅድስት (4)

የጌታዬ እናት ምስጋና ይገባሻል

ከሴቶች ሁሉ አንቺን መርጦሻል

እልል እልል ደስ ይበለን (2)

ወልድ ተወልዶ ነፃ ወጣን

ዮሐንስ ሲያጠምቀው ድል አገኘን

18. † ውስተ ማኅፀነ †

ውስተ ማኅፀነ ድንግል ኀደረ ማኅፀነ ድንግል (፪)

ሰማይ ወምድር ዘኢያገምሮ (፪) በማይ ተጠምቀ (፪)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

In the name of the father the son and the holy spirit one God Amen !

19. † ክርስቶስ ተወልደ †

ክርስቶስ ተወልደ ክርስቶስ ተጠምቀ ክርስቶስ ተወልደ (፪)

ወለደነ ዳግመ (፪) እም መንፈስ ቅዱስ ወማይ (፪)

20. † ኑኑ እንደሰት†

ኑኑ እግደሰት (2)

ጌታ ተጠመቀ (4) ተጠመቀ በዮርዳኖስ (2)

21. † ከድንግል ተወልዶ †

ከድንግል ተወልዶ እኛን ሊቀድስ

ተጠመቀ ኢየሱስ ባህረ ዮርዳኖስ

መጥምቁ ዮሐንስ ምንኛ ታደለ

ከነቢያት ሁሉ ሥልጣኑ ከፍ አለ

አዝ ----------

ትንቢቱን ሊፈጽም አስቦ ክርስቶስ

ተጠምቆ አዳነን በባህረ ዮርዳኖስ

አዝ----------

ምሥጢረ ሥላሴ ታየ የዚያን ለታ

ምን ይከፈለዋል ለአምላክ ውለታ

አዝ ----------

እመቤቴ ማርያም ምንኛ ታደለች

ከአዳም ልጆች ሁሉ አንቺን ተመረጥሽ

አዝ ----------

ቸሩ አምላካችን መድኃኔዓለም

ኑ እናመስግነው በአንድነት ሆነን

22.† የዓለምን በደል †

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ

ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ

ጽድቅን ለመፈጸም በደልን አጥፍቶ

የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ

አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ

የሰማዮች ሰማይ የማይችለውን ንጉሥ

ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ

ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደፈረስ

አዝ ----------

ባህር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ

ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ

እንደተናገረው ዳዊት በትንቢቱ

አዝ ----------

ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሰርት

መጣ በደመና ሰማያዊው አባት

እየመሰከረ የልጁን ጌትነት

አዝ----------

እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ

መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ

አዝ ----------

ባህር ስትጨነቅ ተራራው ሲዘምር

ሰማዩ ሲከፈት ደመናው ሲናገር

ዓለም በዛሬው ቀን አየች ታላቅ ምሥጢር

23. † ጥምቀተ ባህር †

ጥምቀተ ባህር ዮርዳኖስ ነያ (2)

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ (2)

ጌታችን ሲጠመቅ ባህር ምን አለች

አልችለውም ብላ ወደ ኃላ ሸሸች

ብርሃነ መለኮት በወንዙ ሲሞላ

ዮርዳኖስም ሸሸች ሄደ ወደ ኃላ

አዝ ----------

አብ በመጣ ጊዜ ደመናውን ጭኖ

መንፈስ ቅዱስ ታየ በርግብ አምሳል ሆኖ

ለልጁ ምስክር ሊሰጥ ፈለገና

ቃሉን ተናገረ ሆኖ በደመና

አዝ ----------

ጌታችን ሲጠመቅ በ 30 ዓመት

ባሕር ኮበለለች ግዑዟ ፍጥረት

ሰማይ ተከፈተ ሆነልን ፀአዳ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

In the name of the father the son and the holy spirit one God Amen !

ምሥጢረ ሥላሴ ታወቀ ተረዳ

አዝ ----------

እልል በይ ዮርዳንስ የጥምቀት መገኛ

የጽድቅ መሠላል ድህነታችን ለእኛ

ቀላያት አብርህት በዙዎች እያሉ

እንደምን ተመረጥሽ ዮርዳኖስ ከሁሉ

24.† ነፃነት አገኘን †

በዛሬው ጥምቀቱ እሰይ እሰይ ተነግሮ አዋጅ እሰይ እሰይ

ነፃነት አገኘን እሰይ እሰይ በእግዚአብሔር አብ ልጅ

ኧኸ እሰይ እሰይ ተወለደ (2)

ከሰማየ ሰማያት ወረደ

በቅዱስ ዮሐንስ ተጠመቀ

አብ መሰከረለት እሰይ እሰይ በደመና ሳለ እሰይ እሰይ

የምወደው ልጄ እሰይ እሰይ ይኼነው እያለ እሰይ እሰይ

አዝ ----------

ጌታ በዮሐንስ እሰይ እሰይ ሊጠመቅ ሲል ገና እሰይ እሰይ

ወደ ታላ ሸሸ እሰይ እሰይ ዮርዳኖስ ፈራና እሰይ እሰይ

አዝ ----------

እንደ አንበሳ ደቦል እሰይ እሰይ ተራሮች ዘለሉ እሰይ እሰይ

ዕፁብ ነው ድንቅ ነው እሰይ እሰይ

ግሩም ነው እያሉ እሰይ እሰይ

አዝ----------

ውኃን ወይን አረገ እሰይ እሰይ ከተጠራበት ቤት እሰይ እሰይ

የብርሃናት ጌታ እሰይ እሰይ የዓለም መድኃኒት እሰይ እሰይ

25. † ተአምረ ወመንክረ †

ተአምረ ወመንክረ ገብረ መድኃኒነ (2)

በቃና ዘገሊላ ዘገሊላ ከብካብ ኮነ (፪)

26. † በቃና ዘገሊላ †

በቃና ዘገሊላ (፪)

ዘገሊላ ከብካብ ኮነ (፪)×፬

27.† ወረደ መንፈስ ቅዱስ †

ወረደ መንፈስ ቅዱስ (፪)×፬

ቤተ ቃና ዘወይን (፪) ዘወይን (፪) ቤተ ቃና ዘወይን (፪)

28. † እንዘ ስውር †

እንዘ ስውር እምኔነ ይእዜሰ ክሡተ ኮነ (፪)

ተአምረ ወመንክረ ገብረ መድኃኒነ

በቃና ዘገሊላ ከብካብ ኮነ ማየ ረሰየ ወይነ (፪)

29. † ጎዲጎ ተሰዓ †

ጎዲጎ ተሰዓ እኸ ወተሰዓተ ነገደ (2)

ማዕከለ ባሕር (2) እኸ ቆመ ማዕከለ ባሕር(2)

ጌታችን ተጠምቆ በዮሐንስ እጅ

የኃጢያት ደብዳቤ ቀደደ በአዋጅ

ባህረ ዮርዳኖስ መቆም ተስኗት

ሸሸች ወደ ታላ ከመለኮት ፊት

አዝ ----------

ቀላያት ዘለሉ ዕፅዋት ዘመሩ

አንደበት አገኙ ግዑዛን አወሩ

የልጁን ጌትነት ክብሩን ሊያስረዳ

በደመና መጣ አብም ተሰናዳ

አዝ----------

ከወደ ላይ መጣ ምሥጢር ያለው ቃል

የምወደው ልጄን እርሱን ስሙት ሲል

አደለን ዳግመኛ ሁለተኛ ልደት

ከጎኑ በወጣው በማየ ሕይወት ጥምቀት

አዝ ----------

ዘጠና ዘጠኙን መላእክትን ትቶ

በዮርዳኖስ ቆመ አምላክ በአትሕቶ

ማድነቅ ይገባናል የውኃን ሥርዓት

በዓሉ ዛሬ ነው ቃናና ጥምቀት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

In the name of the father the son and the holy spirit one God Amen !